*1

**ክፍት ጥሪ ##2024-03**

**‘ፕሮፋይልስ ኢን ኢምፓክት’**
**ማህበረሰባዊ መፍትሄዎች ለማግኘት የማህበረሰባዊ ፍላጎት ግምገማ**
**የወጣበት ቀን፡ ዲሴምበር 11, 2023**
**አዲስ ማስገቢያ ቀን፡ ፌብርዋሪ 16, 2024**

ታሪክ

የሞንትጎመሪ የምክር ቤት

የካውንቲው የአካባቢ አስተዳደር ቦርድ፣ የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትብብር ምክር ቤት፣ የልጆች፣ የወጣቶችና የቤተሰቦችን ደህንነት ለማጠናከር ከአካባቢው የመንግስት ኤጀንሲዎችና የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ጋር በመተባበር ከባድ ሚና ይጫወታል። ልጆቻችንንና ቤተሰቦቻችን የሚያስፈልጋቸውንና መሰናክል የሚሆንባቸውን ለማወቅ በየሶስት ዓመቱ የማህበረሰብ ፍላጎት ግምገማ እናደርጋለን። ፕሮግራሞችን በገንዘብ በመደገፍ፣ ትብብርን በማዳበርና ለለውጥ በመቆም ስርዓቱን ማጠናከር ኣላማችን ነው። አሁን የ2023 የፍላጎት ግምገማውን እያኪያሄድን ነው።

ስለ ሞንትጎመሪ ካውንቲ የትብብር ምክር ቤት፣ ሥራዎቹና ፕሮግራሞቹ ተጨማሪ መረጃ በ collaborationcouncil.org ድረ ገጽ ይጎብኙ

የማህበረሰብ ፍላጎት ግምገማ

- ይህ ፕሮግራም ብዙ መሰረታዊ ግምቶች አሉት።
- መንትጎመሪ ካውንቲ የሚገኙ ጥቁርና ቡናማ ማህበረሰቦቻችን የሚያገኙት ከሌሎቹ ያልተመጣጠነ ጥሩ ቤት፣ መዋዕለ ህፃናት፣ ምግብ፣ ጤንነትን መንከባከቢያ ፣ መጓጓዣ፣ ደህንንታቸው የተጠበቁ ኣካባቢዎች፣ የትምህርት እድሎችና የትምህርት ቤት በኋላ ፕሮግራሞች ለማግኘት ብዙ መሰናክል እንደሚያጋጥማቸው
- እስከ አሁን ለመፍታት ስንወስዳቸው የነበሩት እርምጃዎች ዘላቂ ለውጥ እንዳላመጡ፣
  ዘላቂ ለውጥ ለማምጣት ከማህበረሰቡ አባላት ጋር ችግራቸውንና መፍትሄውን መወያየት

- የ**2023** የማህበረሰቡ ፍላጎት ግምገማ ለሚከተሉት ገንዘብ በመስጠት ማህበረሰባዊ መፍትሄዎችን ይደግፋል
    - የቤተሰብ ቁጠባን ማጠናከር
    - ለወጣቶች ከሥራና ከትምህርት ጋር ያለውን ግንኙነት ማጠናከር
    - የአየር ጤና በተመለከተ
    - ቅድመ ትምህርትና የእናቶች ጤንነት

ክፍት መጥርያ

የትብብር ምክር ቤቱ የማህበረሰቡን ፍላጎት ለመፍታት እንቅስቃሴዎች ላይ ለመሳተፍ የሚፈልጉ ድርጅቶችና ግለሰቦች የፍላጎት ደብዳቤ ወይም የቪድዮ መልእክት እንዲልኩ ጥሪ ያደርጋል። የትብብር ምክር ቤቱ የተመረጡትን አመልካቾች የማህበረሰቡ ፍላጎት ግምገማ ውስጥ ያካትታቸዋል እንዲሁም የማህበረሰቡን ችግር ለመፍታት ልዩ ራእያቸውን ለመሞከር የ***$10,000*** ኢምፓክት ገንዘብ ይሰጣቸዋል።

ማመልከት የሚችሉት

የማህበረሰቡን ችግር ለመፍታት ከመደበኛ መንገድ ውጪ መፍትሄ ያላቸው ግለሰቦች፣ ድርጅቶችና ፣ ማህበሮች ማመልከት ይችላሉ። ቅድምያ የሚስጣቸው፣ ማህበረሰቡ ውስጥ ያሉ፣ መፍትሄው ማህበረሰቡን የሚያካትት ከሆነ ወይም አበዳሪዎች በልምድ የማያበድርዋቸውን ነው። የበጎ ኣድራጎት ድርጅት ፣ ኤል ኤል ሲ፣ ሶል ፕሮፕራይቶር፣ ገለሰብና **501(c)(3)** ስፖንሰር ያለው ማህበር ሊሆን ይችላል።

ለማመልከት:

- ሞንትጎሞሪ ሜሪላንድ ከማህበረሰቡ ጋር ሆኖ ማህበረሰባዊ መፍትሄ ላይ የሚሰራ፣
- የሜርላንድ ሃላፊነታቸውን እንደተወጡ መረጃ የሚያሳዩ ወይም የሜርላንድ ሃላፊነታቸውን የተወጡ ስፖንሰር ያደረጓቸው

የማመልከቻ ሂደት

ለመወዳደር አመልካች የፍላጎት መግለጫ ደብዳቤ  ወይም  የፍላጎት መግለጫ መልእክት መላክ ኣለባቸው። የሚላከው ከ5 ገጽ ያልበለጠ ወይም በቪድዮ የሚቀጥሉትን ጥያቄዎች በመመለስ ከ፭ ደቂቃ በአልበለጠ ቪድዮ መላክ ይቻላል።

1. ማንኖት? ማንን ነው የሚወክሉት?  የሚያደርጉትን እንድያደርጉ የሚገፋፋዎት ምንድን ነው? በሂደትዎ ላይ ከማን ጋር ይሰራሉ?
2. ድርጅት፣  ማህበር ፣ ሶል ፕሮፕራይተር?
3. ከማን ጋር በሽርክነት እንደሚሰሩና በምን እንደምትሻረኩ በጥልቅ ይናገሩ።
4. የማህበረሰብ ትስስር ሞዴልዎ ምን ይመስላል?  ስለአቀራረብዎ እባክዎትን ይንገሩን።
5. የትኛውን ፍላጎት ለማሟላት ነው የሚሞክሩት?
6. ለችግሩ መደበኛ መፍትሄው ምንድን ነው? የእርሶን የሚለየው ምንድን ነው?
7. **$10,000** እንዴት አድርገው ለመጠቀም ያስባሉ?
8. ለሚያገለግሉት ማህበረሰብ ስኬት ሲባል ምን ይመስላል?

ማመልከቻ ማስገቢያ ቀን

ፌብርዋሪ **16, 2024,  5:00pm**

የፍላጎት ደብዳቤውም ቢሆን፣ የቪድዮ ፍላጎት መልእክቱም፣ ከበላይ ላሉት ጥያቄዎች ለተሰጡት መልሶች  ነጥብ ይሰጣቸዋል። ለመልሶች የተሰጡት ነጥቦቹን፣   ከበታች ያሉትን እንዴት እንደሚያሳዩ ታይቶ አመልካቾቹ በደረጃ ይቀመጣሉ

- ፕሮግራሙ ማህበረሰቡን  እንዴት እንደሚጠቅሙት
- ከማህበረሰቡ ጋር የተሰሩ ሞዴሎችና የፕሮግራሙ አቀራረብ
- ልዩ የሆነ ፣ ግኝትና የትብብር አቀራረብ
- የለውጥ ማስረጃዎች የፕሮግራሙ ስፋት ፣ የሚገለገሉት ወጣቶች/ቤተሰቦች ብዛት፣ የአገልግሎቱ ደረጃ፣ ድግግሞሹና ጥልቀቱን ያጠቃለለ  ወይም ሌላ ለውጡን የሚያሳይ ዳታ።
- የፕሮግራሙ ቦታና፣
- የባጀቱ ተገቢነት / ወጪ

የትብብር ምክር አባላትና የማህበረሰቡ ኢጋሮች  በጋራ ማመልከቻዎቹን ይመለከታሉ።

ለማመልከት  ሊገባ የሚችል አካውንት ይክፈቱና መመርያውን here በዚህ መልክ ይከተሉ።

**ቀጥሎ**

**ለቃለ-መጠይቅ የሚጠሩት አመልካቾች በማርች 1, 2024 ይነገራቸዋል።  የተመረጡት የተቀበልናቸው ማመልከቻዎች ማርች 2024 መጨረሻው ላይ ይነገራቸዋል።**